ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ
Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)

# መግለጫ

## በዴሞክራሲ የማያምን በየቀኑ በዴሞክራሲ ይምላል፣

በሰሜን አሜሪካ ከፊሉ የቅንጅት ልዑከን ቡድን ጥቅምት 7 ቀን 2000 ዓ.ም.ያወጣውን መግለጫ ይመለከታል::

1ኛ) ቡድኑ የቅንጂት አመራር ከእስር ከተለቀቀ ወዲህ በጋራ አመራር መርህ መሠረት ዉሳኔዎችን ሲያስተላልፍ እንደቆየ በማስመሰል መግለጫ ሰጥቷል::

- አመራሩ ከእስር ከተለቀቀ ጊዜ ጀምሮ እነዚህ ጥቂት ግለሰቦች ለዛሬዉ ደባቸዉ ይጠቅሙናል የሚሏቸዉን ግለሰቦች በማግባባት ከእስር የተፈቱ 19 የላዕላይ ም/ቤት አባላትን ብቻ በማሰባሰብ «ዉሳኔዎችን» አሳልፈዋል::

የቅንጅት ላዕላይ ም/ቤት አባላት 60 መሆናቸዉ እየታወቀ 19 ያህሉን ብቻ በማሰባሰብ ለመወሰን መሞከር ከቅንጅት የአሠራርና የስብሰባ መርህ ዉጪ ነዉ:: በህገ ደንባችን መሠረት ምልዓተ ጉባኤዉ 50%+1 ማለትም ቢያንስ 31 አባላት መገኘት ሲገባቸዉ ያለ ምልአተ ጉባኤ በጥቂት ሰዎች የተወሰነዉ ህገወጥ ነዉ::

- ከሁሉም በላይ የፓርቲዉ ጠቅላላ ጉባኤ ፈቅዶና ሕዝብ አዉቆት የቅንጅት ላእላይ ም/ቤት አባላት የሆኑትን ወንድሞቻችንን የታሠረና ያልታሠረ በማለት የእርስ በእርስ አለመግባባትንና መከፋፈል እንዲከሰት ተደርጓል:: እረ ለመሆኑ ያልታሠረ የቅንጅት አመራር በዉሳኔ ላይ እንዳይገኝ የሚገድብ የቅንጅት ህገ ደንብ አለ? በጭራሽ የለም::

- በእነዚህ ጥቂት ግለሰቦች በተካሄዱ ስብሰባዎች ላይ የቅንጅት ፕሬዚዳንት እንጅነር ኃይሉ ሻዉል በህመም ምክንያት ያልተገኙ መሆናቸዉ የተረጋገጠ ነዉ:: እነዚህ ስብሰባዎች ብዙኃኑን ያላካተቱ የጥቂቶች የድብብቆሽ መድረኮች እንጂ በጋራ አመራር መርህ ላይ የተመሠረቱ አልነበሩም::

2ኛ/ ይኸዉ አናሣ ቡድን «የዉጭ አገር ጉዞዎችን እቅድ አወጣሁ» ባለበት ወቅት ፕሬዚዳንቱ ከጉዞ በፊት ቅድሚያ ሊሰጣቸዉ የሚገቡ ድርጅታዊ ተግባራት እንዳሉ በጽሁፍ አስታዉቀዋል::

8605 Cameron Street, Suite M-0, Silver Spring, MD 20910
Tel. (301)565-7864, Fax: 301-565-7863 Email: kinijitusa@kinijit.org

ከእነዚህም መካከል፡-

ሀ. ከሁሉም በፊት የቅንጅት ህልዉና በቅድሚያ በይፋ መረጋገጥ እንደሚገባዉ ለዚህም የድርጅቱ አመራር ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ እዳለበት አሳስበዋል።

ለ. የቅንጅት አመራር ለወህኒ በተዳረገበት ወቅትም ሆነ ከዚያ በፊት የህይወት፣ የአካልና የንብረት መስዋዕትነት ለከፈለዉ የትግሉ ባለቤት ለሆነዉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምስጋና ማቅረብና መወያየት የሚቻልባቸዉን መድረኮች ማመቻቸት እንደሚገባ ጠይቀዋል።

ሐ. ወደ አሜሪካ ከመጓዝ በፊት በትግሉ ወቅት ህይወታቸዉን ካጡት ወገኖቻችን ቤተሰቦች ጋር በመገናኘት የቅንጅት አመራር የሀዘናቸዉ ተካፋይ መሆኑን መግለጽና ማጽጽናናት እደሚገባ ጠይቀዋል።

መ. ከእሥር የወጡትንና ያልታሠሩትን የቅንጅት ላዕላይ ም/ቤት አባላት በማሰባሰብ አመራሩን ማጠናከርና ሥራ ማስጀመር ቅድሚያ ሊሰጠዉ እንደሚገባም አሳስበዋል።

ሆኖም ግን የቡድኑ አባላት እነዚህን አፋጣኝና አስገዳጅ ጉዳዮች ወደጎን በመተዉ ወደ አሜሪካ መምጣትን በመምረጣቸዉ ለወቅቱ ችግሮቻችን መባባሻ ምክንያቶችን አበርክተዋል።

3ኛ/ ቅንጅት ዓለም አቀፍ ም/ቤት (KIC) ቀደም ሲል እንዲያከናዉን የተሰጠዉ የፖለቲካ አመራር መስጠት ዉክልና እዲቀነስ፣ የማደራጀት ሥራዉን ግን አጠናክሮ እንዲቀጥል ተወሰነ እንጂ እንዲፈርስ አልተወሰነም። በወቅቱ ይህን በተመለከተ በፕሬዝዳንቱ ፊርማ የተሰጠዉን መመሪያ በማመሳከር ማረጋገጥ ይቻላል።

4ኛ/ ይህ ሁሉ ሆኖ ለቅንጅት አመራር አንድነት ሲባል ለኢትዮጵያችንም ሆነ ለቅንጅት የላቀ አስተዋጽኦ ያደረጉት የድርጅቱ ፕሬዚደንት በወቅቱ ካደረባቸዉ ሕመም እስኪያገግሙ ድረስ ለቀናት እንዲጠብቋቸዉ ተጠናክረዉ በጋራ የሚጓዙበት መንገድ እንዲመቻች አጥብቀዉ ቢጠይቁም ቡድኑ የእርሳቸዉን መታመም እንደአጋጣሚ እድል በመጠቀም ከእርሳቸዉ ተለይቶ መጓዝን መርጧል።

ዛሬ ፕሬዝዳንቱ ቡድኑን አልፈልግም ያሉ በማስመሰል «ከእኛ ጋር ሊሠሩ አልፈለጉም» ማለታቸዉ ለምን ይሆን? አብረዋቸዉ የታገሉትን፣ መከራና ስቃይ የከፈሉትን መሪያቸዉንና ታላቅ ወንድማቸዉን ወደ ኋላ በመተዉ፣ ወገን በመለየት ትተዋቸዉ ወደ አሜሪካ ለመጓዝ የተሯሯጡት ለምን ይሆን?

የቡድኑን አባላት «መሪዎቻችን» መጡ ብሎ የዋሽንግተንና አካባቢዉ ሕዝብ እንደተቀበላቸዉ ያዉቃሉ። እነርሱስ መሪያችን መጣ ብዉ ኢንጅነር ኃይሉን መቀበል አልነበረባቸዉምን? መመራትን ያላወቀ መሪነትን እንዴት ያዉቃል? እዚሁ ዋሽንግተን ተቀምጠዉ መሪዉን ሊቀበል ከወጣዉ ሕዝብ ጋር ለመቆም ያለመፈለጋቸዉ ወገነኛነትን ከማሣየት ዉጭ ምን ሊባል ይችላል?

5ኛ/ የቡድኑ አባላት ባወጡት መግለጫ ላይ የቅንጅትን ህገደንብ እየደጋገሙ ለመጥቀስ ሞክረዋል:: ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረዉ 19ኙ የላዕላይ ም/ቤት አባላት እነርሱ ብቻ ተሰብስበዉ አሳለፍን የሚሉት ዉሣኔ ሁሉ ህጋዊ አይደለም:: ምልዓተ ጉባዔ ባልተሟላበት ያዉም በአመራሩ መካከል የታሠሩ ያልታሠሩ የሚል ክፍፍልን የፈጠረ ስብሰባ ዉሳኔ በምንም መስፈርት ህጋዊም ዲሞክራሲያዊም አይደለም:: የጋራ አመራር መርህ የጥቂቶች የቡድን ስሜትና ደባ ማስፈጸሚያ ከቶ ሊሆንም አይችልም::

በቅንጅት ደንብ መሠረት የቅንጅት ላዕላይ ም/ቤትና የሥራ አስፈጻሚዉ ኮሚቲ ተሰብስቦ ዉሳኔ መስጠት ባልቻለበት፣ አስቸኳዋይና አጣዳፊ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ፕሬዝዳንቱ የመወሰን ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑም ሊታወቅ ይገባል::

6ኛ/ በአሁኑ ወቅት እየታየ ያለዉ የጥቂት ግለሰቦች ማፈንገጥ የሚያረጋግጠዉ ወደፊት ገሀድ ሊሆን የሚችለዉን በህዝብ ወገንና በሌላዉ ወገን መካከል ሊፈጠር የሚችለዉን ትግል ዉስብስብነት ነዉ::

ሌላዉ አስገራሚዉና አስደናቂዉ ጉዳይ እዉነትን ለሕዝብ ለማሳወቅ ሀቅን ተሸክመዉ፣ ለሀቅ ቆመዉ ወደ አሜሪካ የመጡትን የቅንጅት አመራር አባላት በመቃወም ለማጣጣል መሞከራቸዉ ነዉ:: እዉነት ተደብቃ መቅረት አለባትን? በእኛ በኩል እነዚህ አባላት ሀቅን ወደ አደባባይ ለማዉጣት የሚያደርጉትን ጥረት እንዲገፉበት እናበረታታለን፣ «ያለ እኛ ሰዉ የለም» የሚል አጉል አስተሳሰብን የሚያራምዱ ወገኖችም ወደ ኋላ ዞር ብለዉ እንዲያስቡ እንመክራለን::

በእኛ በኩል በዲሞክራሲና የጋራ አመራር መማልና መገዘት ብቻዉን ዋጋ የለዉም እንላለን:: ሥራችን ከተግባራችን ጋር ሲዋሃድ እንደሚገባም ቡድኑ እናምናለን::

ቡድኑ ወደ አገራችን ስንመለስ ፓርቲዉ ጉዳዩን መርምሮ ዉሳኔ ይሰጥበታል ሲል በመግለጫዉ የጠቀሰዉ በእኛም በኩል ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያለዉ፣ እጅግ የምናምንበትና የምንታገልለት መሆኑንም በዚህ አጋጣሚ ለማረጋገጥ እንወዳለን::

ቡድኑ በአሁኑ ወቅት ከጀመረዉ አፍራሽ ጎዳና ታቅቦ የፓርቲያችንን አንድነትና ጥንካሬ የሚያረጋግጡ፣መተማመንና መግባባትን የሚያመጡ ተግባራትን እንዲያልምም አጥብቀን እናሳስባለን::

መላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የቅንጅት አባላት ደጋፊዎችና ወዳጆቻችን ሁሉ ጉዳዩን በትዕግሥት እንዲከታተሉ አደራ እንላለን::

**ቅንጅት አንድ ነዉ!**
**ኢትዮጵያም አንድ ናት!**

## ቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ፓርቲ

*ጥቅምት 8 ቀን 2000 ዓ.ም*
*ዋሽንግተን፣ ዲሲ*

**8605 Cameron Street, Suite M-0, Silver Spring, MD 20910**
**Tel. (301)565-7864, Fax: 301-565-7863 Email: kinijitusa@kinijit.org**